# የACPS Express 2/24/2023: የመጨረሻ-ዕድል — ፍትሃዊ-እኩልነት ማሳያ (Equity Climate) የዳሰሳ-ጥናት፣ እሁድ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 26 ቀን ይዘጋል

## የመጨረሻ-ዕድል: ፍትሃዊ-እኩልነትን ማሳያ (Equity Climate) - የዳሰሳ-ጥናት፣ እሁድ (Feb.) 26 ቀን ይዘጋል




በሦስተኛው ዓመታዊ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) Equity for all Climate Survey፤ በ11:59 p.m. እሁድ ፌብሩዋሪ (Feb.) 26 ቀን 2023 ከመዘጋቱ-በፊት፣ ከእናንተ እንደምንሰማ ተስፋ-አለን። የእናንተ አስተያየት ዋጋ ያለው እና በACPS ውስጥ  ለሁሉም እኩል የሆነ የመማር አካባቢን ለማሳካት በሚያደርገው-ጥረት -ላይ ከ2025 Strategic Plan ጋር ከተቀመጡት-ግቦች ጋር ሆኖ ለመርዳት፣ ጥቅም-ላይ ይውላል።

የዳሰሳ-ጥናቱ፤ የተማሪውን ስኬት-ላይ መድረስ ለማረጋገጥ ጠንክረን-በምንሰራበት ጊዜ፣ በመማር ላይ የሚኖሩ እንቅፋቶች ላይ ምላሽ-በመስጠት ቀጣይነት-ያለው ዓላማችን ላይ - ወሳኝ-የሆነ ክፍል አለው። የዳሰሳ-ጥናቱ፤ ለሁሉም ከpreK-12 ቤተሰቦች፣ ሠራተኞች፣ እና ከ6-12 ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፤ በትምህርት ቤት ክፍል/school division ውስጥ - በተማሪ መማር፣ በማህበራዊ ስሜታዊነት እርዳታ እና ደህንነት-ላይ ጨምሮ፣ ባሉት ነገሮች ዙሪያ፣ ያላቸውን አመለካከል-ለመስጠት ክፍት-ይሆናል።

የዳሰሳ-ጥናቱ፣ እስከ 30 የሚደርሱ ጥያቄዎች ጨምሮ፤ እና ሞልቶ-ለማጠናቀቅ፣ ከ10-15 ደቂቃዎችን የሚወስድ ይሆናል። ገለልተኛ-የሆነ ሦስተኛ-ወገን የሆነ-ድርጅት - የዳሰሳ-ጥናቱን የሚያስተዳድር፣ እና ሁሉም ምላሾች በሚስጢራዊነት የሚያዙም ይሆናል። የዳሰሳ ጥናቱ፣ በኦንላይን፤ በእንግሊዘኛ፣ በስፓኒሽ፣ በዳሪ፣ በአማርኛ እና በአረብኛ ቋንቋዎች ይገኛል።

የዳሰሳ-ጥናቱን ለማጠናቀቅ እርዳታ-ለማግኘት፤ ጠቃሚ-የሆኑ ትዕዛዞችን የሚያሳየውን ቪዲዮዎች፣ በእንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ አማርኛ እና በአረብኛ እባካችሁ ተመልከቱ። ድምፃችሁ እንዴት ልዩነትን እንደሚያመጣ የበለጠ ለማወቅ፤ በሁለቱም በእንግሊዘኛ እና በስፓኒሽ - ያሉትን ቪዲዮዎቻችንን ተመልከቷቸው።

## አስተያየታችሁን/Feedback አጋሩ: የጦር-መሣሪያ መመርመሪያ መሣሪያ፣ የዳሰሳ-ጥናት



አጭር-የሆነ፤ የማህበረሰብ ትሣትፎ የዳሰሳ-ጥናት - የጦር-መሣሪያዎችን መመርመሪያ መሣሪያ (equipment)ን በአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ የመጠቀም-ሁኔታ በተመለከተ፤ ከአሁን-ጀምሮ እስከ ማርች (March) 8 ቀን 2023 ድረስ እንዲካሄድ ሆኖ-ተከፍቷል። ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ ቤተሰቦች እና የማህበረሰብ አባላቶች፤ ያላቸውን አስተያየቶች እንዲያጋሩ-ተጋብዘዋል። ያላችሁን ሃሳብ እንድታጋሩን፣ ዛሬውኑ - ጥቂት ደቂቃዎችን ወስዳችሁ፤ ይህን አጭር-የዳሰሳ ጥናት - እባካችሁ ሙሉ። የዳሰሳ-ጥናቱ፤ በእንግሊዘኛ፣ በስፓኒሽ፣ በዳሪ፣ በአማርኛ እና በአረብኛ ቋንቋዎች ይገኛል።

“በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ - የጦር-መሣሪያዎች መመርመሪያ መሣሪያን መጠቀም፣ የጦር-መሣሪያዎች ወደ ትምህርት ቤት ተቋማቶቻችን የመግባት-ሁኔታውን ለመቀነስ የሚረዳን-ይሆናል፤” ብለዋል - የተቋማት እና የክንውኖች ብለዋል ሹም፣ ዶ/ር አሊሲአ ሃርት (Dr. Alicia Hart)። ወደ ትምህርት ቤቶቻችን የሚገቡ የጦር-መሣሪያዎች ለመቀነስ-ማስቻል፤ ለተማሪዎች፣ ሠራተኞች እና ጎብኚ-እንግዶች፣ ደህንነቱ-የተጠበቀ የመማሪያ አካባቢዎችን መኖሩን ለማረጋገጥ የሚረዳ-ነው።

የዚህ የመመርመሪያ ዘዴ - በአሁኑ-ጊዜ ያለው ስሪቶች/Current versions የሚያካትተው፤ ፎተግራፍን-ተጠቅሞ - በግለሰቡ ላይ የጦር-መሣሪያዎች ማስፈራሪያ መኖሩንና-አለመኖሩን የሚለይ-ነው። ዘዴው፤ ዘልቆ-ማየት የሚያስችል ሲሆን፤ ከቦርሳዎች ውስጥ ዕቃዎችን ማውጣት የማያስፈልግ እና ግለሰቦች በመደበኛ የእርምጃ-አካሄዳቸው ተረምደው የሚያልፉበት ነው። በፌብሩዋሪ (Feb.) 2 ቀን 2023 ስብሰባው ላይ፤ የትምህርት ቤት ቦርድ፤ የማህበረሰብ ተሣትፎ የዳሰሳ-ጥናትን - ስለዚህ ቴክኖሎጂ በክፍል/division ትምህርት ቤቶች ውስጥ ስለመጠቀም ያለውን-ስጋት-ለማወቅ እንዲካሄድ ፈቃድ-ሰጥቷል። የሚቀጥለው እርምጃ-የሚሆነው፤ የፓይለት ፕሮግራም/pilot program - በACHS-ኪንግ ስትሪት (King Street)፣ ACHS-ሚኔ ሃዋርድ (Minnie Howard)፣ በጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት፣ እና በፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ካፓሶች ማድረግ-ይሆናል።

## ቪዲዮ: የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን - ተቀላቀሉ!




በፌብሩዋሪ (Feb.) 16 ቀን 2023 ላይ በተደረገው የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ላይ፣ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - በሚያስጀምረው የቅጥር-ምልመላ - ርዕሱ፤ “Join Our Equity Journey: ‘Live’። ‘Impact’። ‘Grow’።” በሆነው-ላይ፤ ከአንድ-ደቂቃ ቪዲዮ ጋር፣ የአምስት የACPS ተቀጣሪ-ሠራተኞች - በACPS ውስጥ መስራት-ምን እንደሚመስል በቅንጭብ-እይታን የሰጡበትን ተከትሎ፤ የመጀመሩን-ስራ አብስረዋል። ይህ ቪዲዮ፤ ልዩ የሆነውን ማህበረሰባችንን፣ ስብጥር-ያለውን የተማሪ ቁጥርን፣ ሙያዊ የመማር ዕድሎችን እና ተጨማሪዎች አጉልቶ-ያሳየ ነው።

ይህ ቪዲዮ፤ ACPS ከሚጠቀማቸው ከብዙ ስልቶቹ መካከል አንዱ ሆኖ፤ ከፍተኛ የሙያ-ብቃት ያላቸውን ሠራተኞች በሃገር-አቀፍ የአስተማሪዎች እጥረት ባለበት ወቅት ለመቅጠት ይጠቀመዋል። በ2022-23 የትምህርት ዓመት መጀመሪያ-ላይ፤ አዲስ የትዊተር-አካውንታችንን የሆነውን @ACPSK12Careers አስተዋውቀን-ነበር። ACPS፣ በተጨማሪም በቅርብ-ጊዜ የ‘partnership with George Washington University’s (GW) Graduate School of Education and Human Development’ን አስተዋውቆ-ነበር።

በተጨማሪም፤ እጩ-ሊሆኑ የሚችሉትን አመልካቾች ከ35 በላይ በሆኑ መጪዎቹ የስራ-ፍለጋ ትዕይንቶች፣ ላይ - የባለሁለት ቋንቋ (Dual-Language) የምልመላ ትዕይንት/Recruitment Fair በሆነውን - የማርች (March) 18 ቀን 2023ን-ጨምሮ - ለማግኘት በጉጉት እንጠባበቃለን። የACPS የሰው-ልጅ የመገኛ ምንጮች (Human Resources) ሠራተኞች፤ ሃዋርድ ዩኒቨርስቲ፣ የሜሪላን-ኢስተርን ሾር (Maryland-Eastern Shore) እና ‘The College of William & Mary’ን ጨምሮ በርካታ-ቁጥር ያላቸውን ኮሌጆች ይጎበኛሉ። ACPS፤ በፌብሩዋሪ (Feb.) 18 ቀን 2023 ላይ ከ150 በላይ እጩዎች ወደ ክፍሉ - በዓመቱ የመጀመሪያው-በሆነው የርቀት ፈቃድ-የተሰጣቸው የስራ-መስክ ትዕይንት የተቀበለ-እና፤ በፌብሩዋሪ (Feb.) 23 ቀን 2023 ላይ፣ በአካል-ተገኝቶ (in-person) - ለሁሉም ክፍት የሆነ ዝግጅት (Open House) - የ‘Security Careers’ አዘጋጅቷል።

በACPS አብሮ በመስራት እና በፍትሃዊ ጉዞአችህ ውስጥ ለመቀላቀል ፍላጎት-አላችሁ? ዛሬውኑ፤ ክፍት - ወደሆኑት የስራ-ቦታዎች በኦንላይን ፖርታላችን አማካኝነት አመልክቱ።

## መጪው - የማርች (March) ወር - ክንውን: የማህበረሰብ ተሣትፎ እና የቀን-መቁጠሪያ (Calendar)፣ ማስታወሻዎች

**Community Outreach**
**& CALENDAR REMINDERS**

ለማርች (March) ወር፤ ስለ የቀን-መቁጠሪያ (Calendar) ማስታወሻዎች እና ስለ መጪዎቹ የማህበረሰብ ዝግጅቶች፤ እወቁ። የACPS የማህበረሰብ ሁሉን-የሚያዳርስ (Community Outreach) ቡድን፤ በእናንተ አጎራባች-አካባቢ - መቼ እንደሚገኙ እወቁ!

**ESL II — የመነጋገሪያ ክለብ (Conversation Club)፣ ለመካከለኛ-ደረጃ (Intermediate) ‘ESL’ ተናጋሪዎች**
በማርች (March) ወር ውስጥ - ዘወትር ሰኞ ቀናት፣ እና ሮብ ቀናት ላይ (ማርች/March 1, 6, 8, 13, 15, 20, 22, 27)፤ ከ5:30-6:30 p.m.
ቻርልስ ኢ. ቢትሊ (Charles E. Beatley Jr.) Central Library (5005 Duke St.)
የአሌክሳንድርያ የመጽሐፍት-ቤት (Library)፤ የመማር፣ የመዳሰስ፣ የመፍጠር እና ግንኙነት-ማድረጊያ ዕድሎችን በመፍጠር - ማህበረሰብን ይገነባል። የ‘ESL II Conversation Club’፣ ለመካከለኛ-ደረጃ ላይ ያሉ ተናጋሪዎች (intermediate speakers)፣ እንግሊዘኛ ቋንቋን ልምምድ እንዲያደርጉ እና በራስ-መተማመናቸውን እንዲገነቡ የሚያገለግል-ቦታ ነው። ምዝገባ፣ አያስፈልግም።

**2023 Alexandria፣ የቅዱስ ፓሪክ ቀን ፐሬድ/St. Patrick’s Day Parade**
ቅዳሜ፤ ማርች (March) 4 ቀን 2023 በ12:30 p.m.
300 King Street
በየዓመቱ፤ በማርች (March) ወር ውስጥ፣ በመጀመሪያ ቅዳሜ-ቀን ላይ የሚካሄድ፤ የአሌክሳንድርያ የ‘St. Patrick’s Day Parade’ በኦንልድ-ታውን አሌክሳንድርያ/Old Town Alexandria ውስጥ - እያደገ የመጣ፣ ትልቁ የአንድ-ቀን ዝግጅት ነው። ፐሬዱ (The parade)፤ ‘pipe bands’፣ የ‘Irish dance’ ትምህርት ቤቶችን፣ የማህበረሰብ ቡድኖችን የሚያሳይ እና፣ የሌላ ሙዚቀኞች እና ዝግጅቶችን የሚቀርብበት-ነው። ከቤተሰብ እና ከጓደኞች ጋር ለማሳለፍ፤ ግሩም-የሆነ ቀን ነው።

**ALIVE! ለአጭር-ጊዜ ብቅ የሚሉ የምግብ ማከፋፈያዎች (Pop-Up Food Distributions)**
ሐሙስ፤ ማርች (March) 9 ቀን፣ ከ4:30 -6 p.m.
ዊሊያም ራምዚ (William Ramsay) ማዕከል/Recreation Center (5650 Sanger Ave)
አርብ፣ ማርች (March) 10 ቀን ከ4:30-6 p.m.
ካሳ ቺሪላጉዋ/Casa Chirilagua (4109 Mt. Vernon Ave)
ALIVE!፤ የአካባቢው ለትርፍ-የማይሰራ ድርጅት (not-for-profit organization) ሲሆን፤ በድህንነት ለሚኖሩ የተራቡ - በአሌክሳንድርያ ከተማ ውስጥ የሚገኙ - ልጆች፣ ቤተሰቦች እና ግለሰቦች፣ የአስቸኳይ-ጊዜ እና መሠረታዊ ፍላጎቶችን በመስጠት በትጋት የሚሠራ ነው።
ALIVE! ምግብ-የያዙ ከረጢቶችን (bags)፣ ለአሌክሳንድርያ ከተማ ነዋሪዎች ያከፋፍላል። ምንም፣ መታወቂያ (ID) አያስፈልግም።

**The Woman King**
አርብ፤ ማርች (March) 10 ቀን፤ ከ2-4:30 p.m.
Ellen Coolidge Burke Branch Library (4701 Seminary Rd)
የአንድ-ወር ርዝመት ያለውን የሴቶች ታሪክ (Women's History) ወር - አንዱ-አካል ሆኖ፤ የአሌክሳንድርያ የመጽሐፍት-ቤት (Library) ይህን ታሪካዊ የሆነ አክሽን ድራማ የሆነውን ፊልም - ሴቶች ትዋጊ ወታደሮች - መንግስታቸውን ከጎረቤት ጠላት ለመከላከል ያደረጉትን ህብረት የሚያሳይ ፊልምን ያሳያል። ይህ ፊልም፤ ዕድሜያቸው ከ13 ዓመት በታች ለሆኑ ልጆች - ተስማሚ-ላይሆን ይችላል።

**የአሌክሳንድርያ ፌስቲቫል: ረመዳን/Ramadan -** رمضان مبارك
ቅዳሜ፤ ማርች (March) 11 ቀን ከ2-4 p.m.
ቻርልስ ኢ. ቢትሊ ጁኒየር (Charles E. Beatley Jr.) ማዕከላዊ መጽሐፍት-ቤት (5005 Duke St)
የረመዳን/Ramadan ትርጉምን ለመፈተሽ፣ በአሌክሳንድርያ መጽሐፍት-ቤት በ 'crafts'፣ እንቅስቃሴዎች እና ይህን የዓመቱን ልዩ የሆነ ጊዜን የሚያንጸባርቁ የሚቀማመሱ-ነገሮችን (refreshments) በማግኘት - ከእኛ-ጋር እንሰብሰብ።

**የመካከለኛ (Middle) ደረጃ ትምህርት ቤት - ለሁሉም ክፍት የሆነ ዝግጅት (Open House) ወደ ስድስተኛ ክፍል ለሚያልፉ - ቤተሰቦች**
ማክሰኞ፤ ማርች (March) 21 ቀን፣ ከ9-10:30 a.m. (ጆርጅ ዋሽንግተን/George Washington መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት)
ማክሰኞ፤ ማርች (March). 21 ቀን፣ ከ9-10 a.m. (ፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ/Francis C. Hammond መካከለኛ (Middle) ደረጃ ትምህርት ቤት)
የ2023-24 የትምህርት ዓመት ላይ ምልከታ ከማድረግ ጥቅም-እንዲያገኙ - እና ስለሚሰጡት ኮርስ፣ ፕሮግራሞች፣ ዕድሎች፣ እገዛዎች እና ከትምህርት ቤት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎች/extracurricular activities ለማወቅ - የወደፊት ወላጆች እና ቤተሰቦች ተጋብዘዋል።

**መረጃ-ማግኘት(Information) = መከላከያ-ማድረግ (Prevention): የወላጅ አውደ-ጥናቶች (Workshops) - በአደንዛዥ-ዕፅ አለአግባብ-መጠቀም ላይ**
ሮብ፣ ማርች (March) 22 ቀን፣ ከ6:30-8 p.m.
*በስፓኒሽ-ቋንቋ - ከእንግሊዘኛ ትርጉም-ሰጪዎች አገልጎት ጋር የሚከናወን
በዙም/Zoom አማካኝነት-አብራችሁን ተካፈሉ
ሐሙስ፤ ማርች (March) 30 ቀን፣ ከ6:30-8 p.m.
*ከበርካታ-ቋንቋዎች የትርጉም-አገልግሎት ከሚሰጥበት ጋር - በእንግሊዘኛ-ቋንቋ የሚደረግ
ፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ/Middle ደረጃ ትምህርት ቤት (4646 Seminary Road)
ልጅዎ ዕፆችን ወይም አልኮል-መጠጥን መጠቀምና አለመጠቀሙን እንዴት-ማወቅ እንደሚችሉ ያውቃሉን? ከ6-12ኛ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ የ'ACPS' ተማሪዎች-ወላጆች፤ በተማሪ አገልግሎት እና ፍትሃዊ እኩልነት መምሪያ (Department of Student Services & Equity) እና በቤተሰብ እና ማህበረሰብ ተሣትፎ ማዕከል (Family and Community Engagement Center) - ስለ በአሁኑ-ጊዜ ስላለው የዕፅ መዛመት፣ የሚታዩ ጠቋሚ-ምልክቶች፣ እና የአደንዛዥ-ዕፅ አለአግባብ መጠቀም ምልክቶቹ-ምን እንደሆኑ እና ለቤተሰቦች ስለሚገኙ የመረጃ-ምንጮች የበለጠ-ለማወቅ አብረውን-እንዲካፈሉ ይበረታታሉ።

**የሠራተኛ የሙያ-ማሳደጊያ ቀን (Staff Development Day)**
ሰኞ፣ ማርች (March) 13 ቀን
ለACPS ተማሪዎች፤ ትምህርት አይኖርም።

**የአስተማሪ የሥራ-ቀን/Teacher Work Day**
አርብ፤ ማርች (March) 24 ቀን
ለACPS ተማሪዎች ትምህርት የለም።

**መጪው - የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባዎች**

- **ሐሙስ፣ ማርች (March). 2 ቀን በ6:30 p.m.:** በመደበኛነት-የጊዜ ሰሌዳ የተያዘለት የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ፣ ይካሄዳል።
- **ሐሙስ፣ ማርች (March) 16 ቀን፣ በ6:30 p.m.:** በመደበኛነት-የጊዜ ሰሌዳ የተያዘለት የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ፣ ይካሄዳል።
- **ሐሙስ፣ ማርች (March) 30 ቀን፣ በ6:30 p.m.:** በመደበኛነት-የጊዜ ሰሌዳ የተያዘለት የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ፣ ይካሄዳል።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባዎች፤ በአካል-ተገኝቶ በትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ ክፍሎች ውስጥ - በ1340 Braddock Place ውስጥ - ሌላ ማስታወቂያ-ካልተሰጠ በስተቀረ፣ ይካሄዳል። የማህበረሰብ የህዝብ አባላቶች፣ በአካል-ተገኝተው (in person) ወይም በዙም/Zoom አማካኝነት፣ መሳተፍ ይችላሉ። በስብሰባ የጊዜ-ሰሌዳ ላይ ሊኖሩ ስለሚችሉ ማንኛውም አዲስና-ማሻሻያዎች (updates)፤ በSchool Board webpage ላይ እባካችሁ - ጎብኙ።

## ለ'Black History Month' ስፖት-ላይት/Spotlight የሆነ ተማሪ: የACHS የቲያትር መምሪያ/Theatre Department



ለማህበራዊ ፍትህ-አሰጣጥ (Social justice) መድረክ-የሆነው፤ በአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) የቲያትር መምሪያ/Theatre Department እና በACHS የጥቁር ተማሪ ማኅበር (Black Student Union (BSU) መካከል ካለው ትብብር የበለጠ-ሆኖ አድጓል። ሁሉትም ቡድኖች - በአንድነት ሆነው-በመምጣት - በአሌክሳንድርያ ማህበረሰብ የመታሰቢያ ፕሮጀት - Alexandria Community Remembrance Project በሆነው-በዓለፈው ዓመት ውስጥ፤ ተካፍለዋል። የቅርብ-ጊዜ የትብብር-ማከናወኛ ጥረት የሆነው፤ የ'Black History Month' የ'ብላክ ቦክስ/Black Box' የሌክቸር ተከታታይ-ክፍሎች ነው። የዚህ ዓመት መገለጫ-ገጽታ የሆነው፤ "Black Resistance, Remembrance and 21st Century Revolution" ነው።

"በጥቁር ተማሪዎች ማህበር (Black Student Union) አማካኝነት፣ ይህን ግሩም የሆነ የተማሪዎች ቡድን እና አድቫይዘሮች - ለACHS ተማሪዎች እና ተጋባዥ ሌክቸር-ሰጪዎች - ሐቀኛ-የሆኑ፣ በእውነት-ላይ የተመሰረቱ እና ዐይን-ከፋች የሆኑ - በማህበራዊ ደረጃ ሊያነቃ የሚችሉ ንግግሮችን፣ በምላሹ-ሊሰጥ የሚችለውን እያንዳንዱን በዚህ ሕይወትን ቀያሩ በሆነው ተሞክሮ ውስጥ የሚሳተፉን እያንዳንዳቸውን ሰዎች መቀየር የሚችል ቦታን ያቀርባሉ፤" ብለዋል፤ የACHS የእንግሊዘኛ ቋንቋ እና የቴያቲር አስተማሪ - ሌስሊ ጆንስ (Leslie A. Jones)።

እነዚህ፤ ሁሉን-አሳታፊ የሆኑ በተጋባዥ ተናጋሪዎች፣ በተማሪዎች እና በአስተማሪዎች መካከል የተደረጉ ውይይቶች፤ ርዕሶችን የሚሸፍኑት፤ ባለፈው በልግ (fall) የ‘Student Remembrance Project Pilgrimage to Montgomery fall Alabama’ ዶኩሜንታሪን ጨምሮ - ያካተቱ ናቸው።

“የ‘ብላክ ቦክስ/Black Box’ የሌክቸር ተከታታይ-ክፍል የሚናገረው፤ በሁሉም ጥናቶቻችን፣ በታሪካችን ምክንያት የምርምር-ስራዎችናችን ለበለጠ የጥራት ደረጃ እንዲበቃ ለማስቻል - በአንድ-ላይ ከተሰባሰበው ታሪካችን ጋር ተሳትፎ የማድረግን ጠቃሚነት - የሚናገር-ነው፤” ብለዋል የACHS - የመንግስት እና የታሪክ አስተማሪ ራ አሊም ሻባዝ (Ra Alim Shabazz) - ለ‘Black History Month’ ዕቅድ-አውጪ ኮሚቴ ሊቀመንበርም ናቸው።

ኔታን ደስታ (Nathan Desta)፣ የ‘BSU’ ዋና የቦርድ አባል እና ተማሪ ተዋናይ፤ “BSU እና የ‘Black Box Theatre’ - ለጥቁር ተማሪዎች - እንደ-የሰው ልጅነታቸው ለሚያስፈልጓቸው ነገሮች ብቁ-መሆናቸውን የሚያሳውቅ ነው” ብሎ ያምናል።

የተማሪ የመድረክ አስተዳዳሪ የሆኑት ካተሪን ቢክቴል (Katherine Bectel) ሲናገሩ፤ የጥቁርን ታሪኮች ከፍ-ከፍ የማድረጊያ መንገድ-ሆኖ፤ ከቲያትር መምሪያው ጋር አጋነትን ካስቀመጥን ጀምሮ፤ እንደ “Facing Our Truth: የ10 ደቂቃ - በTrayvon, Race, and Privilege ላይ የቀረበ’ን እና “Chicken & Biscuits” ያሉትን ለቀረፃ-አቅርቧል። “እንደ ቲያትር እና ‘BSU’ ያሉት-ስሜት መግለጫ ቦታዎች፤ ለተማሪዎች ያላቸውን ሃሳቦች ለመግለጽ እና ለውጥን ለማድረግ መድረክ የሚሰጥ-ነው፣” ብለዋል ቢክቴል (Bectel)።

ተቀባይነት የሌለው የነጭ-የበላይነትን እና በሌላ-ሁኔታ ውስጥ አደገኛነት እና አለአግባብ-አተረጓጎም ሊሰጠው የሚችል  - ልብን-ሰባሪ የሆኑ ንግግሮችን፤ በቲያትር/play ውስጥ የመናገሪያ በርካታ-መንገዶች-አሉ፤” ብላለች-  ያህኔ-ማሪ ሳንጋሬ (Yahney-Marie Sangare) - የBSU ምክትል ፕሬዚዳንት እና የተማሪ ተዋናይ። እርሳቸውም ሲናገሩ፤ ‘BSU’ እና ‘Black Box Theatre’ ሁለቱም፤ ለጥቁር ተማሪዎች ደህንነቱ-የተጠበቀ የመሰባሰቢያ ቦታን ፈጥሮላቸዋል፤ እና የ‘Black History Month’ - “የጥቁር ትረካዎች እና ታሪኮች - አድናቆትን እንዲያገኙ እና መደበኛ በሆነ መንገድ እንዲደመጡ መድረክ-ያቀርብላቸዋል፤” ብለው ያምናሉ።

የACHS የቲያትር መምሪያ/Theatre Department፤ በተማሪ-በተፃፈ ቲያትሮች/plays ላይ ለ‘Black History Month’ ታርክን እና ታሪካዊ ጥቁር አርቲስቶችን እንዲሁም የወደፊት የበለጠ ስብጥር-ያለው ቲያትርን ለማሳየት አጉልቶ-ማሳያ ሆኖ ሲሰራ-ቆይቷል።

“ቲያትር፤  አስቸጋሪ የሆኑ ጉዳዮች/difficult subjectsን እና የገጽታ-እይታዎች (themes)ን በሚቀርቡ-ዝግጅቶች እና በመድረክ-አቀራረብ (stagecraft) አማካኝነት - ተማሪዎች መፈተሽ-እንዲችሉ ዕድልን ሰጧቸዋል፤” ብለዋል ቢክቴል (Bectel)። ታሪክን መለስ-ብለን ስንመለከት፤ ተማሪዎች - ለውጦችን በማምጣት ላይ ዋነኛውን ሚና ሁልጊዜ የሚጫወቱ ናቸው፤ ብለዋል። ተማሪዎች - ወደ ተሻለ የወደፊት ሁኔታ እንዲጓዙ ለማድረግ እንዲቻል፤ ስለ ፍትሃዊነት፣ ዘረኝነት እና አድልዎ ባሉ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ መበረታታት አለባቸው - የሚል ስሜት - ቢክቴል (Bectel) አላቸው።

“ተማሪዎች ፍላጎቶቻቸው እንዲሰሙላቸው እና እንክብካቤ-እንዲደረግላቸው ይፈልጋሉ፤ ምክንያቱም -  ለእኛ በአሁኑ-ጊዜ፣ እንክብካቤ ሳይደረግልን እና አድናቆት ሳይሰጠን፤ እንዴት ነው፣ የእኛን የወደፊት-ሕይወታችንን መፍጠር እና ማስተካከል የሚጠበቅብን፤” በማለት ጨምሯል ደስታ (Desta)።

ተማሪዎች የሚገነዘቡት፤ የወደፊት ማንነታቸው ለመግለጽ፣ “ድምፆቻቸው” እንዲሰማ ማድረግ አለባቸው።

“ራስን-በመቻል እና በእውነተኛነት በመናገር ላይ - ለተማሪዎች ኃይልና-ጉልበት እንዲያገኙ ማድረግ፤ ሌሎች ሊያይዋቸው ያልቻሉዋቸውን - የተወሰኑ ጉዳዮች ወደየሚታዩበት-ቦታ እንዲመጡ ያደርጋቸዋል፤” ብላለች ሳንጋሬ (Sangare)። ቢክቴል (Bectel) ጨምረው-ሲናገሩ፤ ለሁሉም ፍትሃዊ-እኩልነት የማስገኛ ክፍሉ፤ በአንድ-ቡድን ላይ ወይም ተመጣጣኝነት-በሌለው ሁኔታ ቀለም-ላላቸው ሰዎች (people of color) ተዛማጅ በሆኑ ጉዳዮች ምክንያት በሚደርስ-ጉዳይ ላይ ብቻ ትኩረት የሚያደርግ አይደለም። “ስለ መጓጓዣ ጉዳዮች፣ የኢኮኖሚ ልዩነቶች፣ ከሁለተኛ-ደረጃ በኋላ ትምህርት፣ ወዘተ…፣ ሁሉም ተፅዕኖ የደረሰባቸው እና በዘር-ተፅዕኖ የደረሰባቸው ናቸው።” ብለው ያምናሉ።

የ‘Black History Month’፤ የአፍሪካዊ አሜሪካውያንን - ለአሌክሳንድርያ አጠቃላይ-ስብስብ ውስጥ ለሚገኘው - ባህል፣ አስተዋጽዖ ያደረጉበትን እና፣ ጥቁር አሜሪካውያኖች እንዴት ታሪካዊ እና ቀጣይ-የሆነውን ጭቆና እንደተቋቋሙ እውቅና የሚሰጥበት-ጊዜ ነው። ይህ ወር በተጨማሪም፤ የወደፊት ማህበረሰባችን እኛ የጣልነው አሻራችን - ምን ዓይነት አስተዋጽዖ እንደሚያመጣ ለመመልከት የሚያገለግለን ነው።

“ታሪካችንን ካልተረዳነው፤ ማንነት-የለንም፣ እራን-ማወቅ-አይቻልም እና ማህበረሰብም አይኖርም፤” ብላለች ሳንጋሬ (Sangare)። “ማህበረሰባችን ከአለፈው-አመጣጡ ላይ የተገነባ ነው፣ እና እውቅና-በመስጠት ብቻ ነው - መዳን ሊገኝ የሚችለው” ብለዋል ቢክቴል (Bectel)። የማህበረሰባችንን ታሪክ መረዳት፤ በአዎንታዊ መንገድ ወደፊት ለመጓዝ የሚረዳ-ነው።

“ስለ አለፈው ሁኔታችሁ ማወቅ፣ መገንዘብ እና መማር ሳትችሉ፣ የወደፊት-ሁኔታችሁን መፍጠር እና ማስቀመጥ-አትችሉም፤” ብሏል ደስታ (Desta)።

## በሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሣምንት እና ከዚያ በላይ-በሆነው ወቅት-ላይ፤ ACPS፣ #HereForTheKids ያካሂዳል




የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሣምንት (Public Schools Week)፤ ከፌብሩዋሪ (Feb.) 27 ቀን - ማርች (March) 3 ቀን 2023 ድረስ፤ ቤተሰቦችን፣ ትምህርት-ሰጪዎችን፣ እና የማህበረሰብ አባላቶችን በአንድነት-በማምጣት፤ የሕዝብ-ትምህርት ባለው ትልቅ-ዋጋ ላይ ብርሃን-በማብራት የሚያሳይ ይሆናል። በዚህ ዓመት፤ የሕዝብ ትምህርት ስርዓታችን፤ እንደ #HerefortheKids ዘመቻ/campaign ሆኖ እየተከበረ-ነው።

የሕዝብ ትምህርት ያሉበትን አስቸጋሪ-ፈታኝ ነገሮችን ለመቋቋም፤ በጋራ ኃላፊነቶችን፣ የተረጋገጡ ስልቶችን እና ፕሮግራሞችን ከግምት-ውስጥ ማስገባትን እና በደንብ-የታሰበበትን መፍትሄዎችን ማስተናገድ የሚችል አካባቢን የሚፈልግ-ነው። በሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሣምንት ወቅት፤ የሕዝብ ትምህርት ያለውን ዋጋ እና የስራ-መስክቸውን ተማሪዎች ፍትሃዊ-እኩልነት ያለው ዕድልን እንዲያገኙ እና ከፍተኛ ብቃት-ያላቸው አስተማሪዎች፣ ሠራተኞች እና የመረጃ-ምንጮችን ማግኘት በማረጋገጥ በትጋት የሚሰሩትን - በማመስገን የሚከበርበት ነው።

የNational School Public Relations Association (NSPRA)፤ በሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሣምንት (Public Schools Week) ውስጥ - ዌቢናሮች (webinars)ን እና የትዊተር ቻት (Twitter chat)ን በማዘጋጀት፤ ይሳተፋሉ። የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - የትምህርት ቤት እና የማህበረሰብ ግንኙነቶች ሹም - የሆኑት ጁሊአ በርጎስ (Julia Burgos) - እንደ ‘NSPRA’ ተወካይ - ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ለተሣትፎ የሚያገለግሉ፤ የብሄራዊ የትምህርት አመራሮችን - በ“Advancing Teaching and Learning Post-Pandemic” በሚለው ርዕስ ለሚከናወነው ዊቢናር (webinar) - ማክሰኞ ፌብሩዋሪ (Feb.) 28 ቀን 2023 - ከ 2-3 p.m. ላይ፤ አብረው-ይካፈላሉ። NSPRA's Twitter profile፤ ዌቢናሩ በቀጥታ-ለተመልካቾች እንዲቀርብ - የሚያሰራጭ-ይሆናል።

የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሣምንትን በሚከበርበት-ጊዜ፤ ሁሉም ተማሪዎቻችን - በዛሬው ስብጥር እና አስቸጋሪ-ሁኔታዎች-በበዛበት ዓለም ውስጥ ስኬታማ እንዲሆኑ የሚረዳቸውን - በእኩልነት የሚሰጥ ትምህርትን የማግኘት ዕድል ስላገኙ፤ ACPS ኩራት-ይሰማዋል። የእኛ 2025 Strategic Plan፤ የACPS አዎንታዊ ወደሆነ የክፍል ትምህርት ቤቶች - እንደ ብሄራዊ መሪ በመሆን፣ ከpreK-12 ትምህርትን - ለሁሉም የሚገኝ፣ ድጋፍ-ሰጪ፣ ሁሉንም-ልጆች ወደስኬት እንዲደርሱ የሚያስችላቸው - የመጓዣ-ካርታ/roadmap ነው።

# ለማርች 2 ቀን 2023 - የትምህርት ቤት ቦርድ አጀንዳ



በማርች (March) 2 ቀን 2023 ላይ ባደረገው-ስብሰባ ላይ፣ የትምህርት ቤት ቦርድ፤ የብሄራዊ የቦርድ ሰርተፊኬሽን ያገኙ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) አስተማሪዎችን እውቅና-የሚሰጥ እና በሚከተሉት ርዕሶች ላይ ምላሽ-ይሰጣል:

- የ'Literacy update'።
- የ2023-24 የቀለም-ትምህርት የቀን-መቁጠሪያ አዲስና-ማሻሻያ/update።
- የፖሊሲ አዲስና-ማሻሻያ/update።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘት ትችላላችሁ።

# በፌብሩዋሪ (Feb.) 16 ቀን 2023 - COVID-19 የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት-ደረጃ




እስከ ፌብሩዋሪ (Feb.) 16 ቀን 2023 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - ዝቅተኛ/low ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤  በየ100,000 ሰዎች፣ 52.69 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤  Alexandria COVID-19 dashboard ጎብኙ።

የመረጃ-ስብስቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በፌብሩዋሪ (Feb.) 16 ቀን 2023 ላይ እንደሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (Centers for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቅላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ-ይመለከታል።